# *“ለዓመታት የተገነቡ ቀበሌዎች በ6 ቀናት  ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወደ አመድነት ተቀይረዋል”*

## ኅዳር 1 ቀን 2013 ዓ.ም. በኮንሶ ዞን አካባቢ ባገረሸ ግጭት መነሻነት

## በአካባቢው ስላለው ወቅታዊ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ሁኔታ የተደረገ

## ፈጣን ምርመራ ሪፖርት

**አንኳርና ምክረ ሃሳብ**

ጥቅምት 21 ቀን 2013 ዓ.ም. ኮንሶ ዞን አካባቢ የሚገኘው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አካባቢውን ለቅቆ መውጣቱን ተከትሎ፣ ከኅዳር 1 እስከ ኅዳር 11 ቀን 2013 ዓ.ም. ድረስ በአሌ፣ በኮንሶ ዞን በሰገን ዙሪያ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች፣ በአማሮ ወረዳ ቡኒቲ ቀበሌ፣ እንዲሁም ከኅዳር 6 እስከ ኅዳር 8 ቀን 2013 ዓ.ም. በደራሼ ወረዳ ጋቶ ቀበሌ ተከታታይ ግጭቶች ዳግም ተከስተዋል። የደቡብ ክልል ሰላምና ፀጥታ ቢሮ በሰገን አከባቢ በተፈጠረው የፀጥታ መደፍረስ እና ግጭት 66 ሰዎች መገደላቸውን፣ 39 ሰዎች መቁሰላቸውን እንዲሁም 132 ሺህ 142 ሰዎች መፈናቀላቸውን አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) ከኅዳር 12 ቀን እስከ ኅዳር 16 ቀን 2013 ዓ.ም.  ወደ አካባቢው የክትትል ቡድን ልኮ ምርምራ አድርጓል። የክትትል ቡድኑ በሀይበና እና በአይዴ ቀበሌዎች እንዲሁም በአርባምንጭ፣ በጊዶሌ እና በካራት ከተሞች  በመገኘት ተጎጂዎችንና ቤተሰቦቻቸውን፣ የአይን ምስክሮችንና የተለያዩ የመንግስት አካላትን በማነጋገር፣ እንዲሁም ሌሎች ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ምርመራውን አካሂዷል። ይሁንና ምርመራው በተካሄደበት ወቅት በአካባቢው የተነሳው ግጭት ሙሉ በሙሉ አለመቆሙ በቂ እና ሰፊ ምርመራ ለማድረግ አዳጋች አድርጎታል።

በዚህ ሪፖርት እንደተመለከተው በርካታ ሰዎች በጥቃት ፈጻሚዎች በጭካኔ እና በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል፣ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ እንዲሁም በርካታ ቀበሌዎች ውስጥ መኖሪያ ቤቶች፣ የተሰበሰበን እህል ጨምሮ ንብረት እና የእርሻ ቦታዎች መሉ በሙሉ እና በከፊል በእሳት ወድመዋል።  ከጥቃቱ መሸሽ ያልቻሉ አቅመ ደካማ ሰዎች ቤታቸው ውስጥ እንዳሉ ተቃጥለው የሞቱ እንዳሉ፣ ነገር ግን ወደተቃጠሉት መንደሮች ተመልሰው ጠፍተው የቀሩ ቤተሰቦቻቸውን ሁኔታ የሚያጣሩበት እድል እንኳን እንዳልተፈጠረ ተጎጂዎች ይናገራሉ። ለምሳሌም መሌጋና ዱጋያ ቀበሌ ላይ ከግጭቱ ጋር በተያያዘ ሰዎች የሞቱበትን አሰቃቂ ሁኔታ ሲያስረዱ፣ “አንድ አዛውንት ለመሸሽ ሞክረው አቅም ስላጠራቸው የጭድ ክምር ውስጥ ተደበቁ። ሆኖም አጥቂዎች ደርሰውባቸው አዛውንቱን ከጭድ ክምሩ ጋር አብረው አቃጠሏቸው። እግሩን ታምሞ እቤት ተኝቶ የነበረ ሌላ ሰው ከቤት ወጥቶ መሸሽ ባለመቻሉ አጥቂዎቹ ቤቱ ውስጥ ገብተው በገጀራ ከገደሉት በኋላ ከቤቱ ጋር አብረው በእሳት አቃጥለውታል ” ብለዋል።

ግጭቱ መጠነ ሰፊ የሆነ ሰብአዊ ቀውስ አስከትሏል። የአንድ ቤተሰብ አባላት ወደተለያየ ቦታ ተፈናቅለዋል፣ አንዳንድ ሰዎች የት እንደደረሱ ወይም ምን እንደደረሰባቸው ማወቅ የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ለምሳሌ አንድ ካራት ከተማ የሚገኙ ተጎጂ ከልጆቻቸው  ተለይተው እንደተፈናቀሉ ተናግረዋል።  አርባምንጭ ከተማ የሚገኙ ሌላ ተጎጂ ቤተሰቦቻቸው ወደ ቡርጂ ወረዳ በነያ ወይም ጎበዜ ቀበሌ መፈናቀላቸውን እና መገናኘት አለመቻላቸውን ገልጸዋል። አንድ ሌላ ተጎጂ “አራስ ልጅ ይዤ  ከአካባቢው ከሚሸሸው ሰው ጋር ተደባልቄ ወደ ጊዶሌ መጥቻለሁ፣ ግን ግጭቱ ሲነሳ እቤት ያልነበረው ባለቤቴ የት እንደሄደ ወይም ምን እንደደረሰበት ማወቅ አልቻልኩም” በማለት ያስረዳሉ።

ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ተጎጂዎችና የአካባቢው መስተዳደር አካላት ስለድርጊቱ ፈጻሚዎች የተለያየና የሚቃረን መረጃ ይሰጣሉ። በአንድ በኩል ጥቃት ፈጻሚዎቹ “የጉማይዴ ልዩ ወረዳ መዋቅር ጠያቂ ታጣቂዎች” እንደሆኑ የሚናገሩ የአካባቢው መስተዳድር አካላትና ተጎጂዎች ያሉ ሲሆን፣ በሌላ በኩል  ጥቃት ፈጻሚዎቹ እራሳቸውን “ኮንሲታ” ብለው የሚጠሩና በደቡብ ክልል ልዩ ኃይል የሚደገፉ የኮንሶ ታጣቂዎች መሆናቸውን የሚናገሩ ተጎጂዎችም አሉ። የደቡብ ክልል ልዩ ኃይልና የኮንሶ ዞን አስተዳደር በበኩላቸው አጥቂዎቹ “የጉማይዴ ወረዳ መዋቅር ጠያቂ ኃይል” ነው በማለት ያስረዳሉ። በተጨማሪም የዞኑ አስተዳደር የግጭቱ መነሻ የጉማይዴ ወረዳ መዋቅር ጠያቂ ኃይል በልዩ ኃይል ላይ የወሰደው “የትንኮሳ እርምጃ” መሆኑን ሲገልጽ፣ ልዩ ኃይሉ ደግሞ የደረሰበት ትንኮሳ እንደሌለ ይናገራል። የኮንሶ ዞን አስተዳደር በግጭቱ የደራሼ ወረዳ፣ የኦነግ ሸኔና የሕወሓት እጅ እንዳለበት ሲገልጽ፣ የደራሼ ወረዳ አስተዳደር በበኩሉ የኮንሶ ዞን አስተዳደርን ይከስሳል።

ግጭቱ ሙሉ በሙሉ ብሔር ተኮር ጥቃት  ነው ለማለት ባይቻልም ከአማሮ ወረዳ ቡኒቲ ቀበሌ የተፈናቀሉ የተወሰኑ ተጎጂዎች፣ “አማሮች በአማሮ መሬት ተቀምጠው የጉማይዴን መዋቅር ይደግፋሉ” በሚል ጥቃት የሚያደርሱባቸው አካላት እንዳሉ ይገልጻሉ።

የኮንሶን መዋቅር የሚደግፉ ሰዎች፣ የጉማይዴን ልዩ ወረዳ መዋቅር የሚደግፉ ሰዎች እና በመዋቅሩ ጉዳይ ምንም አይነት ፍላጎት እና አቋም የሌላቸው የየአከባቢው ነዋሪዎች ሁሉም በተመሳሳይ መልኩ የግጭቱ ተጎጂዎች ሆነዋል። የአከባቢው ማኅበረሰብ የብሔር ብዝኃነት ያለው እንደመሆኑ፣ “የጉማይዴን ልዩ ወረዳ መዋቅር ጥያቄ ትደግፋላችሁ” ተብለው የተጠቁ ነገር ግን የብሔር ማንነታቸው

የተለያየ ተጎጂዎች እንዳሉ ሁሉ፣ “የኮንሶን አመራር እና መዋቅር ትደግፋላችሁ” ተብለው ለጥቃት የተጋለጡና የብሔር ማንነታቸው የተለያየ ተጎጂዎችም አሉ።

የችግሩ መሰረታዊ ምክንያት ወይም የስር መንስዔ ገና እልባት ያላገኘና ግጭቱ መልሶ ሊያገረሽ የሚችል በመሆኑ ዘላቂ መፍትሄ የመፈለጉ አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤በአሁኑ ወቅት በግጭቱ ለተፈናቀሉና በተለያዩ አካባቢዎች ተጠልለው ለሚገኙ ሰዎች አስፈላጊውን ሰብአዊ እርዳታ ማድረስ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ቀዳሚው ስራ ነው። የተጎጂዊችንና የተፈናቃዮችን ቁጥር፣ የተፈናቀሉበትን ምክንያትና መንስዔ በግልጽ ማስቀመጡና ማሳወቁ የሰብአዊ እርዳታ ፍላጎቱን መጠን ለመወሰን እንደሚጠቅም ሁሉ ለቀጣይ የፍትሕ ሂደቱ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ነው። ለተፈናቃዮች የሚቀርበው ሰብአዊ እርዳታም ሆነ ተፈናቃዮችን ወደመኖሪያቸው የመመለሱ ስራ ግጭቱ ሰብል በሚሰበሰብበት ወቅት የተከሰተ መሆኑንና በግጭቱ የደረሱና የተሰበሰቡ ማሳዎች መቃጠላቸውን ታሳቢ ሊያደርግ ይገባል።

ለበርካታ ዓመታት ሲንከባለሉ የቆዩና በአብዛኛው ከአስተዳደራዊ መዋቅር ወይም ከአደረጃጀት ጋር የተያያዙ የህዝብ ጥያቄዎች መኖራቸው ግልጽ ነው። ስለሆነም እነዚህን አስተዳደራዊ ጥያቄዎች ቀደም ሲል ግጭት ሲያስነሱ ከነበሩና ከድንበር ወይም ከተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ጋር ከተያያዙ ጥያቄዎች መለየት ያስፈልጋል። እነዚህን አስተዳደራዊ የህዝብ ጥያቄዎች ተገን አድርገው ግጭት የሚያባብሱ እና ድጋፍ የሚያደርጉላቸውን አካላት ተጠያቂነት የማረጋገጡ ሂደት ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ቢሆንም፣ የአካባቢውን ሰላም በዘላቂነት ማረጋገጥ የሚቻለው አስተዳደራዊ ጥያቄዎቹ ግልጽና ህዝቡን ያሳተፈ ምላሽ ሲሰጣቸው ነው።

የመንግስትን መዋቅር ይዘው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግጭቱን የሚያነሳሱ፣ የሚደግፉና የሚያባብሱ ወይም ግጭቱን ባለመከላከል ኃላፊነታቸውን በማይወጡ ሰዎች ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል። በአካባቢው እየተስፋፋ እንደመጣ የሚነገረው የሕገወጥ መሳሪያ ዝውውር ላይ የሚደረገው ቁጥጥር ማጠናከርም በኮንሶ ዞንና በአካባቢው በየጊዜው የሚያገረሹ ግጭቶች ለማስቀረት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ነው።

**ስለኮንሶ (አደረጃጀትና አጠቃላይ አውድ)**

ኮንሶ በኢትዮጵያ ደቡብ ምዕራብ በሰገን ወንዝ አቅራቢያ የሚገኝና ወደ 300 ሺህ የሚገመት ህዝብ የሚኖርበት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ውስጥ የሚገኝ አካባቢ ነው። ኮንሶ ከአርባ ምንጭ 90 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የሚገኝና በደቡብ በቦረና (ኦሮምያ ክልል) በምዕራብ በአሌ ልዩ ወረዳ (ደቡብ ክልል) እና በሰሜን ደራሼና አማሮ ወረዳዎች የሚዋሰኑት አካባቢ ነው። በ2004 ዓ.ም. የኮንሶ ባሕላዊ አሰፋፈርና በአካባቢው የሚገኘው 23 ሺህ ሄክታር የሚገመት ስፋት ያለው የተፈጥሮ ሃብት በዩኔስኮ ዓለምአቀፍ ባሕላዊ ቅርስ በመባል በመመዝገቡ ከኢትዮጵያ ቱሪዝም መዳረሻ አካባቢዎች አንዱ ነው።

ኮንሶ ከ2003 ዓ.ም. እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ 'የሰገን አካባቢ ህዝቦች' በሚል ስያሜ፣ አምስት ወረዳዎችን ያቀፈ (ኮንሶ፣ደራሼ፣አማሮ፣ ቡርጂ እና አሌ) ዞን ስር የሚገኝ መዋቅር ነበር።  የሰገን አካባቢ ህዝቦች ዞን ሲቋቋም የዞኑ ዋና መቀመጫ እንዲሆን አዲስ የከተማ አስተዳደር ተደራጅቶ፣ ከተማ አስተዳዳሩ ከኮንሶ ወረዳ 9 ቀበሌዎችን፣ከቡርጂ ወረዳ 4  ቀበሌዎችን፣ ከአማሮ ወረዳ 3  ቀበሌዎችን እና ከደራሼ ወረዳ 1  ቀበሌን በድምሩ 17 ቀበሌዎችን በመያዝ 'የሰገን ከተማ አስተዳደር' በሚል ስያሜ ተዋቀረ። የሰገን ከተማ አስተዳደር የያዛቸው 17 ቀበሌዎች ከ1987 ዓ/ም በፊት "የጉማይዴ ወረዳ" ተብለው ተዋቅረው የነበሩ ሲሆን ከ1987 ዓ/ም በኋላ ግን ቀበሌዎቹ የብሔር አደረጃጀት ወዳላቸው ወረዳዎች እንዲጠቃለሉ ተደረገ።

ከ2007 ዓ.ም. ጀምሮ ሲነሳ የነበረው የኮንሶ ወረዳ ወደ ዞን አስተዳደር የመቀየር ጥያቄ ከአራት ዓመታት በኋላ በ2011 ዓ.ም. ተፈቀደ። በሰገን አካባቢ ህዝቦች ዞን ስር የሚገኙት ሌሎች ወረዳዎች (ደራሼ፣አማሮ፣ቡርጂ እና አሌ) እያንዳንዳቸው እራሳቸውን የቻሉ ልዩ ወረዳዎች ሆነው እንዲቀጥሉ በመደረጉ፣ 17 ቀበሌዎች ይዞ የነበረው የሰገን ከተማ አስተዳደር በድጋሚ እንዲፈርስና ሁሉም ቀበሌዎች ከ1987 ዓ.ም. እስከ 2003 ዓ.ም. ወደነበሩበት የብሔር አደረጃጀት እንዲጠቃለሉ ተደረገ።

ይህም "የጉማይዴ ወረዳ አግኝቶት የነበረው መዋቅር ሊፈርስ አይገባም" የሚል ቅሬታ እንዲፈጠርና "የጉማይዴ ህዝብ ልዩ ወረዳ አስመላሽ ኮሚቴ" እንዲቋቋም ምክንያት ሆነ። እራሳቸውን እንደ "ጉማይዴ ህዝብ" የሚቆጥሩ እና በ17ቱ ቀበሌዎች የሚገኙ ሰዎች፣ በብሔር አደረጃጀት መሰባጠር እንዳልነበረባቸው፣ "የጉማይዴ ህዝብ ልዩ ወረዳ መዋቅር" በዙሪያው ለሚገኙ ቀበሌዎች ማኅበራዊ አገልግሎት ወይም የመንግስትን አገልግሎት ለመስጠት ምቹ እንደነበረ፣ ህብረተሰቡም የሥነ ልቦና አንድነት እንዳለውና የሚተዳደርበትን ቋንቋም መወሰን ያስቻለው የነበረ በመሆኑ፣ "የሰገን ከተማ አስተዳደርን" ከማፍረስ ይልቅ የልዩ ወረዳ መዋቅር ሊሰጠው እንደሚገባ ይከራከራሉ።

የኮንሶ ዞን፣የአማሮ ወረዳ እና የቡርጂ ወረዳ አስተዳደሮች በበኩላቸው "የጉማይዴ ልዩ ወረዳ መዋቅር እንዲመለስ የሚጠይቀው አካል የራሱ መሬት፣ ህዝብ እና መዋቅር የሌለው መሆኑን፣ እንዲሁም ህዝቡ በአካባቢው ከሚገኙ ብሔረሰቦች የተውጣጣ ህብረተሰብ በመሆኑ የስራና የአስተዳደር ቋንቋ ለመምረጥ እንደሚቸገር በመግለጽ "የጉማይዴን ልዩ ወረዳ መዋቅር" ሃሳብ ይቃወማሉ።

ሰኔ 2011 ዓ.ም. የደቡብ ክልል አስተዳደር 17 ቀበሌዎችን ይዞ የነበረው የሰገን ከተማ አስተዳደር እንዲፈርስ እና ቀበሌዎቹ ቀድሞ ወደነበሩበት ወረዳቸው እንዲጠቃለሉ ውሳኔ አሳለፈ። አካባቢው ለበርካታ ዓመታት የተለያዩ የድንበር ይገባኛል ግጭቶች የሚያገረሹበት የነበር ቢሆንም የሰገን ከተማ አስተዳደር እንዲፈርስ ከተደረገ ጀምሮ "የጉማይዴ ልዩ ወረዳ መዋቅር ጥያቄን" በሚደግፉ እና በሚቃወሙ አካላት መካከል በየጊዜው እየሰፋና እየተወሳሰቡ የሚሄዱ ግጭቶችን እያስተናገደ ይገኛል።

የቀድሞ የሰገን ከተማ አስተዳደር ኮንሶን፣ደራሼን፣ቡርጂን እና አማሮን የሚያዋስን ቦታ እንደመሆኑ ሰገን ከተማ ላይ የሚነሳው ግጭት የእነዚህን አከባቢዎች ህዝብ ሰላምና ፀጥታ እየጎዳ ቆይቷል። ለምሳሌ ኢሰመኮ በኅዳር ወር 2012 ዓ.ም. ባደረገው ምርመራ በተመሳሳይ መንስኤ በአከባቢው በተፈጠረ ግጭት 53 ሰዎች መገደላቸውን እና በንብረት ላይ በግምት ከ40 ሚሊዮን ብር በላይ ጉዳት መድረሱን ሪፖርት አድርጎ ነበር።

***የምርመራው ግኝቶች***

የክስተቱ ሂደት (ኅዳር 4 ቀን እስከ ኅዳር 11 ቀን 2013 ዓ.ም.)

- *መሌጋና ዱጋያ ቀበሌ*

ኅዳር 3 ቀን 2013 ዓ.ም. ከምሽቱ 12 ሰዓት አከባቢ ተኩስ ተጀመረ። ቤቶች በሙሉ ተቃጠሉ። መሮጥና ማምለጥ ያልቻሉ 5 ሰዎችም በአሰቃቂ ሁኔታ በእሳት፣ በቆንጨራ እና በጥይት ተገደሉ።

"ኩሽልቴ የተባሉ የ70 ዓመት ሽማግሌ መሸሽ ሲያቅታቸው ጭድ ውስጥ ገብተው ተደበቁ። አጥቂዎቹ ጭዱን በእሳት ለኩሰው አብረው አቃጠሏቸው። ኩሴ ኮርኔሌ የተባለ ሌላ የ30 ዓመት ወጣት ደግሞ የሚኖርበት ቤት በር ላይ በጥይት መትተውት ስላልሞተ አጥቂዎቹ በቆንጨራ ቆራርጠው ገደሉት። ዳንጎል የተባሉ የ90 ዓመት ሽማግሌ ለመሸሽ የሚያግዛቸው ሰው ስላልነበር እቤታቸው ሲቃጠል አብረው ተቃጥለዋል። ገልገሎ ገዳቶ የተባሉ የ35 ዓመት ወጣት እግሩን ታምሞ ተኝቶ ስለነበር ከቤቱ ጋር አብሮ ተቃጥሎ ሞቷል። ከርበና ቦውጋማ የተባለ የ35 ዓመት ወጣት ለመሸሽ ሲሞክር አጥቂዎቹ ስለደረሱበት ቀጥቅጠው ገድለውታል።" በማለት ተፈናቃዮች የተጎጂዎችን አሟሟት ያስረዳሉ።

የመሌጋና ዱጋያ ቀበሌ ተፈናቃዮች ስለአጥቂዎቹ ማንነት ሁለት የተለያዩ መረጃዎች ያቀርባሉ። አንዳንዶች አጥቂዎቹ የጉማይዴ ወረዳ መዋቅር ጥያቄ ደጋፊዎች መሆናቸው ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ አጥቂዎቹ "ኮንሲታ" የሚባሉ የኮንሶ ሕገወጥ ታጣቂዎች እንደሆኑና የታጣቂዎቹ ቡድን "የጉማይዴ መዋቅርን ትደግፋላችሁ፣  ቦታው የኮንሶ ስለሆነ ለቃችሁ ውጡ" በማለት የተለያዩ ጥቃቶች ሲፈጽምባቸው የቆየ ቡድን መሆኑን ይናገራሉ።

- ሰገን ከተማ

ከሰገን ከተማ የተፈናቀሉ ተጎጂዎች እንደሚሉት “እስከአሁን በሕይወት የቆዩት ከ2011 ዓ.ም. ጀምሮ የመከላከያ ሠራዊት በአካባቢው የሰፈረ በመሆኑ ብቻ ሲሆን” የደቡብ ልዩ ኃይል ግን “ለኮንሶ በመወገን” ድብደባ እና እስር ሲፈጽምባቸው ቆይቷል። ግጭቱ ሲነሳም ከኮንሶ ታጣቂዎች ጋር በማበር ያፈናቀላቸው ይኸው የደቡብ ልዩ ኃይል መሆኑን ይናገራሉ። “የኛ አቤቱታ አይደመጥም፤ ለኛ ከለላ አይሰጥም፤ኮንሶዎች ሲያመለክቱ ግን ያለምንም ማጣራት ልዩ ኃይሉ በእኛ ላይ ድብደባና እስር ይፈጽማል፤ የኮንሶ አስተዳደርም ቢሆን ‘የሰገን ህዝብ የማይታዘዝና የጉማይዴን ወረዳ የሚደግፍ ነው’ በማለት ማህበረሰቡን ለማጥቃት የእህል ወፍጮ ቤቱን ሳይቀር ዘግተውብናል፣ መብራትና ውሃ አቋርጠውብናል፤ ሱቆችን ዘግተውብናል እንዲሁም ገበያ አቋርጠውብናል። ‘ምድሩ የኮንሶ ነው፣ ለምን አፋን ኦሮሞ ወይም አማርኛ ትናገራላችሁ? ለምን ኮንስኛ አትናገሩም? በኮንሶ መገዛት ካልፈለጋችሁ ለቃችሁ ሂዱ’” እንባላለን በማለት ያስረዳሉ።

ተፈናቃዮቹ “በብዙ መልኩ ተበድለን ቆይተን መንግስት ጥያቄያችንን ከአዲሱ የክልል አደረጃጀት ጋር ይመልሳል ብለን ስንጠብቅ ጥቅምት 21 ቀን 2013 ዓ.ም. መከላከያ ሠራዊቱ ከተማውን ለቆ ወጣ።  ኅዳር 4 ቀን 2013 ዓ.ም. ጠዋት ላይ የደቡብ ልዩ ኃይል ‘ያለምንም ምክንያት’ ወደበቾ ቀበሌ ገብቶ ሰዎች ላይ ተኩስ ከፈተ፣ 2 ሰዎችን ገደለ። በዚህም ምክንያት ግጭት ተቀሰቀሰና ግጭቱ በሁሉም ቀበሌዎች ስለተዛመተ ተፈናቀልን” ይላሉ። ሰገን ከተማ ላይ ቃጠሎ ባይደርስም፣ ተኩሱ ከፍተኛ በመሆኑ፣ በአቅራቢያ ያሉ ቀበሌዎች ሲቃጠሉ እሳቱ ይታይ ስለነበር እና  “የሰገንን ህዝብ የኔ ህዝብ ነው ብሎ የሚከላከል አካል ባለመኖሩ” ስጋት አድሮባቸው መፈናቀላቸውን ያስረዳሉ።

“አበራ ኦርካይዶ የሚባል መምኅር የደቡብ ልዩ ኃይሎች ጥይት እየተኮሱ መምጣታቸው ሲነገርና ሰው ሲሸሽ እርሱም ከዋናው መንገድ ዞር ብሎ የሙዝ ዛፍ ስር በተከለለበት በጥይት ተመቶ ተገድሏል። አዲዮ ሀብቴ(ዕድሜ 35 ዓመት) እና ገልገሎ ባሌ የተባለ የ 9 ዓመት ልጅ በጥይት ተመትተው ተገድለዋል። ሃምሳ አለቃ ኢብሳ የተባሉ የቴሌ መስሪያ ቤት የጥበቃ ሰራተኛ ቆስለዋል።”

ከዚህ በተጨማሪም የኮንሶ አመራር ገለልተኛ አካል ወደቦታው እንዳይገባ እና ከህዝቡ ጋር እንዳይገኛኝ “የሽብር ዜና በመፍጠር” የሚከለክል መሆኑንና ህዝቡን ለማወያየት የተለያዩ አካላት በልዩ ሁኔታ ወደቦታው በሚመጡበት ወቅት፣ ወደ ውይይቱ እንዲገቡ የሚፈቀድላቸው ሰዎች “በኮንሶ አመራር የተመረጡ ሰዎች ብቻ” መሆናቸውን ተፈናቃዮች ያስረዳሉ። የጉማይዴን ወረዳ መስተዳድር መዋቅር የሚፈልገው ህዝብ ከሚመለከታቸው የክልል እና የፌደራል ባለሥልጣናት ጋር እንዳይገናኝ ይደረጋል ብለዋል። “በኢትዮጵያዊነታችን እንደ ህዝብ መደራጀት እና የአስተዳደር መዋቅር ማግኘት ነው የጠየቅነው፡፡ ነገር ግን በብሔር ብቻ ነው የምትደራጁት በማለት ህዝቡ ወኪል እና ድምጽ እንዳያገኝ ነው የተደረገው” በማለት ቅሬታቸውን ይገልጻሉ።

በሌላ በኩል የመዋቅር ጥያቄው ላይ ምንም አይነት አስተያየት የሌላቸው እና በሰላም መኖር ብቻ የሚፈልጉ ነዋሪዎች መኖራቸውን ገልጸው የመንግስትን ወይም ማኅበራዊ አገልግሎት ማግኘት እንዳልቻሉ፣ ልጆቻቸውን የማስተማር፣ በነጻነት የመንቀሳቀስ፣ የጤና አገልግሎት የማግኘት፣ የልማት፣ የመስራት እና ከመንግስትን የደኅንነት ጥበቃ የማግኘት መብታቸው ለረጅም ግዜ ተጥሶ ግጭት በተፈጠረ ቁጥር ለመፈናቀል እና ለእንግልት እንደሚዳረጉ፣ እንዲሁም ቤት ንብረታቸው እንደሚወድም አስረድተዋል። በአሁኑ ግጭት “የመዋቅር ጉዳይ ውስጥ አልገባም” በማለት ገለልተኛ ሆነው የሚኖሩ አቶ ኡጋንዴ አንጋሬ የተባሉ የ70 አመት የሀገር ሽማግሌ በጉማይዴ ታጣቂ ቡድን መገደላቸውን ገልጸዋል።

ከዚሁ ከተማ የመጡ ሌሎች ተጎጂዎች ደግሞ ለጥቃት የተጋለጡት የኮንሶን አመራር እና መዋቅር ትደግፋላችሁ በሚል ምክንያት መሆኑንና ወደ ካራት ከተማ የተሰደዱት “በልዩ ኃይሉ እጀባ” መሆኑን ይገልጻሉ። “በቁጥር ለማስቀመጥ የሚያስቸግር ብዛት ያለው ሰው እንደሞተ” እና አስከሬን ለማንሳት አዳጋች እንደሆነባቸው አክለው አስረድተዋል።

- በቾ ቀበሌ

የበቾ ቀበሌ ተፈናቃዮች የግጭቱን መነሻ ሲያስረዱ “ኅዳር 4 ቀን 2013 ዓ.ም. ጠዋት 3፡00 ሰዓት አከባቢ የደቡብ ልዩ ኃይል በመኪና ወደ ቀበሌው ገብቶ፣ በየአቅጣጫው ተኩስ ከፈተ። ልዩ ኃይሉ እቤቷ ውስጥ የነበረችና አያና ኮራ የተባለች የ12 ወይም 13 ዓመት ሕጻን ልጅ እንዲሁም አንድ ይማም ጌቱ የተባለ ጎልማሳ በጥይት መትተው ገደሉ። ከዚያም አካባቢውን ለቅቀው ሄዱ። ሁኔታው ሳይረጋጋ የኮንሶ ታጣቂዎች ‘ከጫካ’ በመውጣት ማሳ ላይ የተከመረ እህል እና ቤት ማቃጠል ጀመሩ። ተኩስ በመከፈትም ዶፋ እንግዳ እና ማርቆስ ዛላ የተባሉ ሁለት ሰዎች ገደሉ። ስለሆነም ህዝቡ አካባቢውን ጥሎ ሸሸ፣ ወደ ሀይበና፣ ጎበዜ እና በነያ ቀበሌያት ተፈናቀለ” ይላሉ።

የኮንሶ አመራር በቾ ላይ ከዚህ ቀደም አንድ የእህል ወፍጮ ቤት አሸጎ እንደነበርም ነዋሪዎቹ ይናገራሉ፡፡

“የኮንሶ አመራር እንደሚለው ጥቃት የሚፈጽሙት ‘የጉማይዴ መዋቅር ደጋፊዎችና የኦነግ ሸኔ ታጣቂዎች’ ከሆኑ፣ የጉማይዴን መዋቅር የሚደግፈው ሰው ለምን ይፈናቀላል? ንብረቱ ለምን ይቃጠላል? ለምን ይገደላል?” በማለት ተጎጂዎች ይሞግታሉ። ይልቁን  “የክልሉ መንግስትም ሆነ ልዩ ኃይሉ “ለኮንሶ ወግኖ” እያሳደዳቸው እንደሆነ ይናገራሉ። “በማሳ ያለ እህል በተከመረመበት ነው እንዲቃጠል የተደረገው። ገለልተኛ የፀጥታ አካል ተመድቦ ወደቀያችን ቢመልሱን እንኳን ህዝቡ የሚበላው ነገር የለም፤ ቀበሌው አመድ ሆኗል፤ በቀጣይ ዓመትም ለረሀብ ተጋላጭ እንድንሆን ተደርጓል። ኮንሶ “ኮንሲታ” የሚባል  ታጣቂ ቡድን አቋቁሟል፡፡ ህዝቡን የሚጨፈጭፈው ይህ አካል ነው፡፡ የሚሳበበው ግን በጉማይዴ ደጋፊዎች ላይ ነው” በማለት ይገልጻሉ።

አንድ ተጎጂም “እኔ የጉማይዴ ልዩ ወረዳ ደጋፊ ነኝ፣ ያፈናቀለኝ የኮንሶ ታጣቂ ነው እንጂ የጉማይዴ ታጣቂ አይደለም። መሳሪያ ቢኖረኝ እራሴን እከላከል ነበር እንጂ ቤተሰብ እና ከብት ይዤ አልሰደድም ነበር” ብለዋል።

- ደራሼ ወረዳ ጋቶ ቀበሌ መንደር 1

በኩሱሜ ብሔረሰብ በኩል ከዚህ በፊት የተጠየቀው የጋቶ ከተማ አስተዳዳር መዋቅር ጥያቄ አለመመለሱ፤ እንዲሁም የደራሼ ወረዳ አስተዳዳር በመንደር 1 ነዋሪዎች ላይ የሚፈጽመው አስተዳደራዊ በደል ቆሞና ቅራኔው ተፈትቶ ህዝቡ እና አመራሩ መካከል መግባባት አለመፈጠሩ በተፈናቃዮች ተገልጿል።

የደራሼ ወረዳ አመራር ለመንደር 1 እርዳታ የመጣ ብር እና እህል ለመስጠት ዳተኝነት ማሳየቱን እንዲሁም ከዚህ ቀደም በነበረ ግጭት የተፈናቀሉ ሰዎችን መልሶ ለማቋቋም ጥረት አለማድረጉን ጨምረው አንስተዋል። የመንደር 1 ነዋሪዎች መንደር 2 ሄደው እርሻ ማረስ እንደማይችሉ እና በሁለቱ መንደሮች መካካል ያለውን ወንዝ በጋራ ከመጠቀም ውጪ ሁለቱ መንደሮች በምንም ጉዳይ እንደማይገናኙ ያስረዳሉ።

ኮሚሽኑ ምርመራ ባካሄደበት ወቅት በአይዴ ቀበሌ የሚገኙ የጋቶ ቀበሌ መንደር 1 ተፈናቃዮች ኅዳር 6 ቀን 2013 ዓ.ም. ከምሽቱ 2 ሰዓት አከባቢ በተፈጠረ ተኩስ እና የእሳት ቃጠሎ የተፈናቀሉ ናቸው። ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ሁኔታ "መንደር 2 እና የደራሼ አመራርና ታጣቂ" በጋራ በመሆን አፈናቅለዋቸው የነበረ መሆኑንና ወደቀዬአቸው ለመመለስም ሆነ ሌላ እርዳታ ሳያገኙ ቆይተው፣ በድጋሚ በተነሳው ግጭት መንደር 1 ሙሉ በሙሉ በመቃጠሉ ወደ ኮንሶ አካባቢ ለመሰደድ መገደዳቸውን ያስረዳሉ። መንግስት ሰብአዊ ድጋፍ እና እርዳታ ያላደረገላቸው መሆኑን እና ያነጋገራቸው አካል አለመኖሩን አክለው ይገልጻሉ። ግጭቱን ማን እንደጀመረው እና ማን እንደተሳተፈበት ባያስረዱም ከ40 በላይ አስከሬን እንደተነሳ አስረድተዋል።

- ካራት ዙሪያ፣ፋጨጫ ቀበሌ

የፋጨጫ ቀበሌ ተፈናቃዮች በበኩላቸው ከላይ የተጠቀሰውና በደራሼ ወረዳ በጋቶ ቀበሌ በደረሰው ችግር ምክንያት "መንደር 2 እና ደራሼዎች" እንዳፈናቀሏቸው የሚናገሩ ናቸው። "ከኅዳር 6 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በፋጨጫ ቀበሌ ግጭት የነበረ ሲሆን፣ በኅዳር 8 ቀን 2013 ዓ.ም. ኮንሶ ክልል ድረስ መጥተው ቤቶቻችንን አቃጠሉ፣ ጥይት ተኩሰው 4 ሰዎች ገደሉ። የተገደሉት ሰዎች ጌታቸው ካሱ፤ ኩሴ ገረሱ፤ታምሩ ኃይሌ እና ፑልዴ የሚባሉ ሴት የአእምሮ ታማሚ ሲሆኑ፣ አቅም ያለው ሰው የቻለውን ያህል ሸሽቷል" ብለዋል። በቦታው ያለው ልዩ ኃይል ጥበቃ ከማድረግ ይልቅ፣ "ለደራሼ በመወገን" እንዳጠቃቸው ይገልጻሉ።

- ሀይሎታ ዶካቱ

"የጉማይዴን መዋቅር ትደግፋላችሁ እያሉ የኮንሶ ታጣቂዎች ሲያፈናቅሉን ይህ ለአምስተኛ ጊዜ ነው። ግጭት ሲነሳ ታጣቂዎቹ በአይሱዙ ነው ወጣቶችን ከሌላ ቦታ የሚያመጡት። ቀደም ሲል ትንሽም ከለላ የሚሰጠን መከላከያ ነበር። ልዩ ኃይሉ ለኮንሶ ወግኖ ሰውን መደብደብ፣ መግረፍ፣ ማሰር ነው ስራው። የኛ አቤቱታ እና ችግር አይፈታም። በሀይሎታ ዶካቱ ቀበሌ ችግሩ የጀመረው መከለከያ ከወጣበት ከጥቅምት 21 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ ነው። ሠራዊቱ አካባቢውን ለቅቆ ሲወጣ፣ ከቀበሌው ተባርረን 'አዲስ ገበሬ' ቀበሌ ለመስፈር ተገደድን። ግጭቱ ሲባባስ ግን ከአዲስ ገበሬ ቀበሌ ለቅቀን ወደተለያየ ቦታ ተበታተንን። ዘረፋ፣ ንብረት ማቃጠል፤ በማሳ ያለ እህል ማቃጠል ተፈጽሞብናል። ነፍሰጡር ሴቶች፣ እናቶች፣ ጨቅላ ሕጻናት፣ አረጋውያን እና እንስሳት ይዘን በመንከራተት ላይ ነን" በማለት ተፈናቃዮች ያስረዳሉ።

- ቡኒቲ ቀበሌ

ግጭቱ የተከሰተው ኅዳር 6 ቀን 2013 ዓ.ም. ሌሊት መሆኑን የቡኒቲ ቀበሌ ተፈናቃዮች ያስረዳሉ። "በሰገን አከባቢ የነበረው መከላከያ ሠራዊት እንደወጣ ከዚህ በፊት ያፈናቀለን የቀበሌ ሊቀመንበር ከተደበቀበት ጫካ ታጣቂዎችን ይዞ ወደ ቀበሌው ገባ። ከዚህ ቀደም ባይናከ በዙ የሚባል ሊቀመንበር በቡኒቲ በሚኖሩ 'አማሮች' ላይ ግድያ፣ንብረት ማውደም፤ አካል ጉዳት እና ማፈናቀል ማድረሱ ተጣርቶ፣ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት ነበር። ነገር ግን ግለሰቡ በቁጥጥር ስር ባለመዋሉ፣የመከላከያ ሠራዊቱ አካባቢውን ለቅቆ ሲወጣ፣ ግለሰቡ ከጫካ በመውጣት ተመሳሳይ ጥቃት ፈጽሟል።(ኢሰመኮ በ2012 ዓ.ም. ባደረገው ምርመራ በወቅቱ ተጠርጣሪው በቁጥጥር ስር አለመዋሉን አረጋግጧል።)

"ባይናከ በዙ ህዝቡን ሰብስቦ 'አማራን አስወጥተን አልነበረም? ለምን ተመለሳችሁ? ማንን ተማምናችሁ ነው የመጣችሁት?' በማለት በስራ ላይ የነበረውን የቀበሌ ሊቀመንበር አስጠርቶ በህዝቡ ፊት ደበደበው፤ መሳሪያውን ቀማውና 'አንተ ለኮሬ ህዝብ አትሆንም፤ ወደፈለክበት ሂድ' በማለት አሰናበተው። በዚህ ሁኔታ እያለን ኅዳር 6 ቀን 2013 ዓ.ም. ሌሊት ቃጠሎ ተጀመረ" በማለት ገልጸዋል።

አንድም ቤት ሳይቀር ቀበሌው ሙሉ በሙሉ በቃጠሎ መውደሙን፣ መሸሽ ያልቻሉ አረጋውያን ከቤቱ ጋር አብረው መቃጠላቸውን እና ማን የት እንዳለ እንደማያውቁ ይናገራሉ። ከቡኒቲ የተፈናቀሉ ሰዎችም በዋናነት ቡርጂ ወረዳ፣ በነያ እና ጎበዜ ቀበሌዎች ላይ እንደሚገኙ ያስረዳሉ። አንድ ተጎጂ እርሳቸው ወደ አርባምንጭ ከተማ ቢሰደዱም ቤተሰቦቻቸው ወደየት እንደተሰደዱ ማወቅ እንዳልቻሉ ይናገራሉ።

የአማሮ ወረዳ አስተዳደር ሰገን ከተማ የተቀሰቀሰው ግጭት ወደ ቡኒቲ ቀበሌ ተዛምቶ ጉዳት ማድረሱን የገለጸ ሲሆን፣ በግጭቱ 9 ሰዎች መሞታቸውን፣ 530 ቤቶች መቃጠላቸውንና 11 ሺህ 786 ሰው መፈናቀሉን አስረድተዋል። ከዚህ በፊት በነበረው ግጭት በወንጀል ክስ ይፈለግ የነበረውን ባይናከ በዙ የተባለ ግለሰብ ለመያዝ የፀጥታ አካሉ በተደጋጋሚ ያደረገው ጥረት አለመሳካቱንና ተጠርጣሪው ሊያዝ እንዳልተቻለ ገልጸዋል።

- ቡርጂ ወረዳ፣ ትንሿ ቀያቴ ቀበሌ እና ደራሼ ወረዳ፣ የሀይበና ቀበሌ አስተዳደር

የትንሿ ቀያቴ ቀበሌ ነዋሪዎች በቀበሌው ግጭት ባይከሰትም አዋሳኝ ቀበሌዎች በእሳት ሲጋዩ የሚታዩ በመሆናቸውና ተኩሱ ረዘም ላለ ጊዜ ሳይበርድ በመቆየቱ እንደተፈናቀሉ ይናገራሉ። በተመሳሳይ መልኩ በሀይበና ቀበሌ ግጭት የተከሰተበት አካባቢ ባይሆንም ከሰገን የተፈናቀሉ ሰዎች መጠለያ ሆኖ እያገለገለ እንደሆነ የቀበሌው አስተዳደር ይገልጻል።

**የአካባቢው አስተዳደርና የሌሎች ኃላፊዎች ምላሽ**

የግጭቱን መነሻ በተመለከተ የኮንሶ ዞን አመራር አባሎች "ኅዳር 3 ቀን 2013 ዓ.ም. ምሽት፣ በሰገን ዙሪያ ወረዳ አዲስ ገበሬ ቀበሌ ላይ በሚገኘው የደቡብ ክልል ልዩ ኃይል ላይ ድንጋይ በመወርወር እና ጥይት በመተኮስ ትንኮሳ ሲፈጸም አደረ። ተንኳሾቹም የጉማይዴ ልዩ ወረዳ መዋቅር ጠያቂ ታጣቂ ቡድን አባላት ሲሆኑ፣ ቡድኑ ትንኮሳውን ከፈጸመ በኋላ ወደ በቾ ቀበሌ እንደገባ መረጃ ስለደረሰ ልዩ ኃይሉ በማግስቱ ጠዋት ወደ በቾ ቀበሌ በመሄድ ከታጣቂው ቡድን ጋር የተኩስ ልውውጥ በማድረጉ ግጭት ተቀሰቀሰ" በማለት ይገልጻሉ።

የደቡብ ክልል ልዩ ኃይል ግን ኅዳር 3 ቀን 2013 ዓ.ም. የተፈጸመበት ትንኮሳ እንደሌለና ኅዳር 4 ቀን 2013 ዓ.ም. ወደ በቾ ቀበሌ እንዳልተንቀሳቀሰ ይናገራል። ይልቁን የአካባቢው ፀጥታ መዋቅር ትኩረቱን በሙሉ "በኮንሶ እና በአሌ መካከል ኅዳር 1 ቀን 2013 ዓ.ም. በተፈጠረው ግጭት" ላይ በማድረጉ ይሄንን ክፍተት ሲጠብቅ የነበረ ጸረ ሰላም አካል ግለሰቦችን በማጥቃት፣ ቤትና በማሳ ያለ እህል በማቃጠል ግጭት እንዲቀሰቀስ ማድረጉን ያስረዳል። ጸረ ሰላም አካል የተባለውም "የጉማይዴ ልዩ ወረዳ ጠያቂ ኮሚቴ" በሚል የተደራጀ እና የታጠቀ ቡድን መሆኑን ገልጿል።

በጋቶ የሚገኘው ልዩ ኃይል በበኩሉ የሚከተለውን ይላል "ኅዳር 5 ቀን 2013 ዓ.ም. መንደር 1 ላይ ያሉ ነዋሪዎች እቃቸውን ይዘው ወደ ኮንሶ በኩል መውጣት መጀመራቸውን ተመለከትን። 'ምን ሆናችሁ?' ብለን ስንጠይቃቸው፣ ሰገን አከባቢ ግጭት ስለተፈጠረ ለደኅንነታቸው እንደሰጉ ነገሩን። በዚያኑ ዕለት ምሽት 3፡00 ሰዓት ሲሆን የአንድ ከተማ ህዝብ የሚያክል ብዛት ያላቸው ሰዎች ያገኙትን ታጥቀው በመንደር 2 ላይ ዘመቱ። እኛም በመከላከል ላይ እያለን የታጠቀው ቡድን በተለያየ መንገድ ውስጥ ውስጡን እያቆራረጠ ወደ መንደር 2 ማቅናቱን ቀጠለ። ይሁንና መንደር 2 ላይ ያለ ሰው እራሱን ከመከላከል አልፎ የመንደር 1 ቤቶች አቃጥሏል። ስለሆነም መንደር 1 ላይ ያለው ህዝብ ወደ ኮንሶ በኩል ተፈናቀለ። ግጭቱ በመንደር 1 እና በመንደር 2 ሰዎች መካከል የደረሰ የእርስ በእርስ ግጭት ነው። 'ህዝብ ሆ' ብሎ ሲወጣ አጥፊውን እና ሰላማዊውን ሰው ለይቶ እርምጃ ለመውሰድ አስቸጋሪ ሁኔታን ይፈጥራል።" በግጭቱ ሰዎች እንደሞቱ መረጃው ቢደረሰውም "ሁለቱም አካላት" የሞቱትን ሰዎች ቁጥር አለማሳወቃቸውን በጋቶ የሚገኘው የልዩ ኃይል አባላቱ አክለው ገልጸዋል።

በተመሳሳይ መልኩ የደራሼ ወረዳ አስተዳዳር ግጭቱ የተጀመረው መንደር አንድ ታጥቆ እና ተደራጅቶ መንደር ሁለትን ለማጥቃት በመሞከሩ እንደሆነ ይገልጻል። የመንደር 1 ነዋሪ የነበሩ ተፈናቃዮች ደግሞ ምሽት ላይ ተኩስ መጀመሩን እና ነዋሪው መሸሽ መጀመሩን እንጂ ግጭቱን ማን እንደጀመረው እንደማያውቁ ተናግረዋል።ይሁንና በአካባቢው መንደር 2 በደራሼ አመራርና በቀበሌው በሚገኘው ልዩ ኃይል፣ መንደር 1 ደግሞ በኮንሶ አመራር ይደገፋል የሚል እምነት መኖሩን ተጎጂዎችም ሆኑ የመንግስት አካላት ያስረዳሉ።

**የሰብአዊ መብቶች ጥሰትና ተጠያቂነት**

የኮንሶን መዋቅር የሚደግፉ ሰዎች፣ የጉማይዴን ልዩ ወረዳ መዋቅር የሚደግፉ ሰዎች እና በመዋቅር ጉዳይ ምንም አይነት ፍላጎት እና አቋም የሌላቸው የየአከባቢው ነዋሪዎች ሁሉም በተመሳሳይ መልኩ የግጭቱ ተጎጂዎች ሆነዋል። የአከባቢው ማኅበረሰብ የብሔር ብዝኃነት ያለው እንደመሆኑ፣ "የጉማይዴን ልዩ ወረዳ መዋቅር ጥያቄ ትደግፋላችሁ" ተብለው የተጠቁ ነገር ግን የብሔር ማንነታቸው የተለያየ ተጎጂዎች እንዳሉ ሁሉ፣ "የኮንሶን አመራር እና መዋቅር ትደግፋላችሁ" ተብለው ለጥቃት የተጋለጡና የብሔር ማንነታቸው የተለያየ ተጎጂዎችም አሉ።

የጉማይዴን መዋቅር የሚደግፉ ተጎጂዎች እራሱን "ኮንሲታ" ብሎ የሰየመ የኮንሶ ሕገወጥ ታጣቂ ቡድን መኖሩንና ቡድኑ በልዩ ኃይል እና በኮንሶ አመራር እየተደገፈ ጥቃት እንደፈጸመባቸው ሲናገሩ በአንጻሩ የኮንሶ ዞን አመራር አባሎች በኮንሶ በኩል የታጠቀ ሕገ ወጥ ቡድን እንደሌለ እና የጉማይዴ ልዩ ወረዳ መዋቅር ጠያቂ ታጣቂዎች ጥቃት ሲፈጽሙ አርሶ አደሩ ተደራጅቶ ባለው መሳሪያ እራሱን የሚከላከል ብቻ መሆኑን ይገልጻሉ። ይልቁን በግጭቶቹ ውስጥ "የአነግ ሸኔና የሕውሓት አባላት የሆኑና ግጭቱ እንዲበርድ የማይፈልጉ የመከላከያ ሠራዊት አመራሮች" እጅ እንዳለበት ያስረዳሉ። የኮንሶ ዞን አመራር የደራሼን ወረዳ አመራር ለጥቃት ፈጻሚዎቹ ድጋፍ በማድረግና ተጠያቂነት እንዳይኖር ሽፋን በመስጠት ይከስሳል። የደራሼ ወረዳ በበኩሉ በተለይ ጋቶ ቀበሌ ያለው ችግር የኮንሶ ዞን አመራሮች እጅ እንዳለበት ይናገራል።

ሰገን ከተማ እና ጋቶ ያለው ልዩ ኃይል እና ፌደራል ፖሊስ ባለው አቅም የመከላከል እና የመቆጣጠር ስራ መስራቱን ነገር ግን የግጭቱ ባሕሪ፣ የሰው ኃይሉ እና ታጣቂዎች የሚጠቀሙት መሳሪያ ከባድ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ግጭቱን ማስቀረት አለመቻሉን ይገልጻሉ። ጥቃት ፈጻሚዎቹን ለመቆጣጠር ጥረት ቢደረግም፤ "ሁሉም ወደጫካ መሸሻቸውን" የገለጹ ሲሆን፣ በአንጻሩ 1 የልዩ ኃይል አባል መሞቱን እና 4 አባላቱ መቁሰላቸውን አሳውቀዋል።

የደቡብ ክልል ሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኅዳር 20 ቀን 2013 ዓ.ም. በሰጠው መግለጫ በአከባቢው ሕግን የማስከበር እና አከባቢውን የማረጋጋት ስራ እየተሰራ መሆኑን እና ተፈናቃዮችን ወደ ቦታቸው ለመመለስ እና ሰብአዊ እርዳታ ለማድረስ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጾ፣ ከግጭቱ ጋር በተገናኘ 137 ተጠርጣሪዎች መታሰራቸውን አሳውቋል።

**ተፈናቃዮች የሚገኙበት ሁኔታ**

በግጭቱ ምክንያት በንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት አጠቃላይ ግምት ገና ለማወቅ ባይቻልም በሰገን ዙሪያ ወረዳ፣ 4 ቀበሌዎች ላይ የሚገኙ ቤቶች፣ በውሳጣቸው ያለው ቁሳቁስ እና በማሳ የሚገኝ የደረሰ ሰብል ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ በእሳት መውደሙን ኮሚሽኑ ተረድቷል። በካራት ዙሪያ ወረዳ፣ ፉጨጫ ቀበሌ እና በአማሮ ወረዳ፣ ቡኒቲ ቀበሌ በተመሳሳይ መልኩ ሙሉ በሙሉ በእሳት ወድመዋል። ተጎጂዎች እና የኮንሶ ዞን አመራሮች "ለአመታት የተገነቡ ቀበሌዎች በ6 ቀን  ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወደ አመድነት ተቀይረዋል" በሚል ክስተቱን ገልጸውታል። በደራሼ ወረዳ ደግሞ ጋቶ ቀበሌ መንደር 1 ሙሉ በሙሉ መቃጠሉ የተመለከተ ሲሆን የጋቶ እና የፉጨጫን ቀበሌዎችን ውድመት ኮሚሽኑ በአካል አይቶ አረጋግጧል። በኮንሶ ዞን ውስጥ ደግሞ ተጨማሪ 6 ቀበሌዎች በከፊል መውደማቸው ታውቋል፡፡

የደቡብ ክልል የሰላምና የፀጥታ ቢሮ እንዳስታወቀው በግጭቱ 132 ሺህ 142 ሰዎች ተፈናቅለው በተለያዩ አካባቢዎች ተበታትነው ይገኛሉ። በደራሼ ወረዳ በኩል በወረዳው የተፈናቀሉ እና የተጠለሉ ተፈናቃዮች መኖራቸው ተገልጿል። ከጋቶ ቀበሌ መንደር 1 የተፈናቀሉ የኩሱሜ ብሔረሰብ አባላት መኖራቸው ተነግሯል።  የጋቶ ቀበሌ መንደር 1 ተፈናቃዮች በሙሉ ወደ ኮንሶ የተፈናቀሉ ሲሆን  ደራሼ እና ኮንሶ፣ በሁለቱም መዋቅሮች በኩል እርዳታ ተጠይቋል። በሌላ በኩል ከኮንሶ ዞን ሰገን ዙሪያ ወረዳ እና ከአማሮ ወረዳ፣ ቡኒቲ ቀበሌ የተፈናቀሉ ሰዎች ቡርጂ ወረዳ፣ በነያ እና ጎበዜ ቀበሌዎች ላይ ይገኛሉ። የኮንሶ ዞን በሌላ ወረዳ የሚገኙትን ሰዎች የማምጣት ስራ ቢጀምርም መንገዱ በታጣቂዎች በመቆረጡ ስራው መቋረጡን ለኮሚሽኑ ክትትል ቡድን አሳውቋል።

በኢሰመኮ ምልከታ እንደታየው ተፈናቃዮች ፈጣን፣ የተቀናጀና የተሟላ የሰብአዊ እርዳታ እያገኙ አይደለም። አርባ ምንጭ ከተማ፣ ካራት ከተማ እና ጊዶሌ ከተማ ላይ መጠነኛ የምግብ፣ የውሃ፣ የመጠለያ፣ የሕጻናት ምግብ እና የቁሳቁስ አቅርቦት ያለ ሲሆን በሀይበና፣ በአይዴ ቀበሌዎች የመጠለያ፣ የምግብ እና የውሃ ችግር ተከስቷል። በሀይበና ቀበሌ አስተዳደር የተጠለሉ ሰዎችን በተመለከተ የቀበሌው አስተዳደር የተፈናቃዮች ቁጥር በርካታ በመሆኑ የውሃ፣ የቀለብ፣ የማደሪያ፣ የመጸዳጃ ቤትና የአልባሳት ችግር እንደገጠማቸው እና የመጣው እርዳታ "የተወሰነ በቆሎ" ብቻ መሆኑን አመልክቷል።

ተፈናቃዮች በተጠለሉባቸው በሁሉም አካባቢዎች የማብሰያ ቁሳቁሶች፣ የአልባሳት፣ የጤና አገልግሎት፣ የመጸዳጃ ቦታ እና የንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁሶች አቅርቦት እንደሌለ ታይቷል። አብዛኞቹ ተፈናቃዮች በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን በአንዳንድ አከባቢዎች በአንድ ክፍል ውስጥ 9 አባወራ እና ከ50 ቤተሰብ በላይ የሚያድሩ በመሆኑ ለኮቪድ ወረርሽኝ መጋለጥ አጋጣሚን የሚጨምር ነው። ነፍሰ ጡር ሴቶች፣ የሚያጠቡ እናቶች፣ ከ5 አመት በታች የሆኑ ሕጻናት እና ወጣት ተፈናቃዮች የሚገኙ ቢሆንም፣ የኮሚሽኑ ምርመራ ቡድን በቦታው እስከነበረበት ጊዜ ድረስ ለተፈናቃዮቹ የተሰጠው ሰብአዊ እርዳታ የነዚህን ህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በሀይበና እና በአይዴ ቀበሌዎች የሚገኙ ተፈናቃዮች ከብቶቻቸውን ጭምር ይዘው ስለተፈናቀሉ የከብቶች መኖ እና ውሃን ለመሳሰሉ ተጨማሪ የአቅርቦት ችግሮች ተጋልጠዋል። ተፈናቃዮች በበኩላቸው እንስሳቶቻቸውን ይዘው ስለተሰደዱ፣ የመኖ እና የውሃ ችግር እንዳጋጠማቸው ገልጸው መንግስት የአከባቢውን ፀጥታ አስከብሮ ወደቀያቸው እንዲመልሳቸው ጠይቀዋል።

**ምክረ ሃሳብ**

- የችግሩ መሰረታዊ ምክንያት ወይም የስር መንስዔ ገና እልባት ያላገኘና ግጭቱ መልሶ ሊያገረሽ የሚችል በመሆኑ ዘላቂ መፍትሄ የመፈለጉ አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤በአሁኑ ወቅት በግጭቱ ለተፈናቀሉና በተለያዩ አካባቢዎች ተጠልለው ለሚገኙ ሰዎች አስፈላጊውን ሰብአዊ እርዳታ ማድረስ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ቀዳሚው ስራ ነው። የተጎጂዊችንና የተፈናቃዮችን ቁጥር፣ የተፈናቀሉበትን ምክንያትና መንስዔ በግልጽ ማስቀመጡና ማሳወቁ የሰብአዊ እርዳታ ፍላጎቱን መጠን ለመወሰን እንደሚጠቅም ሁሉ ለቀጣይ የፍትሕ ሂደቱ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ነው። ለተፈናቃዮች የሚቀርበው ሰብአዊ እርዳታም ሆነ ተፈናቃዮችን ወደመኖሪያቸው የመመለሱ ስራ ግጭቱ ሰብል በሚሰበሰብበት ወቅት የተከሰተ መሆኑንና በግጭቱ የደረሱና የተሰበሰቡ ማሳዎች መቃጠላቸውን ታሳቢ ሊያደርግ ይገባል።

- ለበርካታ ዓመታት ሲንከባለሉ የቆዩና በአብዛኛው ከአስተዳደራዊ መዋቅር ወይም ከአደረጃጀት ጋር የተያያዙ የህዝብ ጥያቄዎች መኖራቸው ግልጽ ነው። ስለሆነም እነዚህን አስተዳደራዊ ጥያቄዎች ቀደም ሲል ግጭት ሲያስነሱ ከነበሩና ከድንበር ወይም ከተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ጋር ከተያያዙ ጥያቄዎች መለየት ያስፈልጋል። እነዚህን አስተዳደራዊ የህዝብ ጥያቄዎች ተገን አድርገው ግጭት የሚያባብሱ እና ድጋፍ የሚያደርጉላቸውን አካላት ተጠያቂነት የማረጋገጡ ሂደት ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ቢሆንም፣ የአካባቢውን ሰላም በዘላቂነት ማረጋገጥ የሚቻለው አስተዳደራዊ ጥያቄዎቹ ግልጽና ህዝቡን ያሳተፈ ምላሽ ሲሰጣቸው ነው።

- የመንግስትን መዋቅር ይዘው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግጭቱን የሚያነሳሱ፣ የሚደግፉና የሚያባብሱ ወይም ግጭቱን ባለመከላከል ኃላፊነታቸውን በማይወጡ ሰዎች ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል። በአካባቢው እየተስፋፋ እንደመጣ የሚነገረው የሕገወጥ መሳሪያ ዝውውር ላይ የሚደረገው ቁጥጥር ማጠናከርም በኮንሶ ዞንና በአካባቢው በየጊዜው የሚያገረሹ ግጭቶች ለማስቀረት የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ነው።